# ሰው ሃይማኖቱን ለምን ይለውጣል?

## በቀሲስ ከፍያለው ጥላሁን

ነሐሴ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም
አዲስ አበባ

# መቅድም

ና

መቅድም ማለት መጀመሪያ ወይም አስቀድሞ የሚገኝ ነው። መቅድም የሌለው መጽሐፍ በር እንደሌለው ቤት ይቆጠራል። በር የሌለው ቤት በውስጡ ያለውን ነገር ገብቶ ለማየትና ለማወቅ አይቻልም እንዲሁም መቅድም የሌለው መጻሕፍንም ደግሞ በውስጡ የያዘውን ሃሳብ በቶሎ ሊ ገባንና ልናውቀው አንችልም። ነገር ግን ሃሳቡ በቶሎ እንዲገባን የመጽሐፉን ጠቅላላ ይዘት በማሳጠር በመቅድሙ ላይ እንዲገለጽ የግድ ያስፈልጋል።

ስለዚህ የዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ዋና ዓላማው የሰው ልጅ በጥንተ ተፈጥሮውና ባሕርያቱ እንዴት እግዚአብሔርን ይመስለዋል? የሰው ውድቀትና ጸጋዎቹን መነጠቁ፣የዲያብሎስ የተንኮል መንገድ፣ከውድቀት በኋላ የሰውን ልጅ ሕይወት የታደገው ማነው? የሚለውን ነጥብ በመጠኑ ይጠ ቁመናል። ከዚህ በተጨማሪ ሰው ሁኖ ተፈጥሮ ኅሊና ካለው ያለ ሃይማኖት ይኖራል ማለት እጅግ ስለሚከብድ ስለትክክለኛው ሃይማኖት ሰዎች እንዲ ረዱና ሰዎች ስለሃይማኖት፣ምግባር፣ሥርዓት ከማን መማር እንደሚገባቸው እየጠቆመ በመጨረሻም ሰዎች ለምን ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ? ለሚለው የዘመኑና የትውልዱ ጥያቄ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርጎ መልስ ይሰጠናል። መልካም ንባብ

«ይህን መጽሐፍ ብላ»

ሕዝ. ፫፥፩



# 1. ሰው ማለት ምን ማለት ነው?

ሰውን የግዕዙ ቋንቋ ሰብእ ይለዋል። ሰው ከሰባት ግብራት የተፈጠረ ነው። ሰባት ግብራት የተባሉት አራቱ ባሕርያተ ሥጋና ሦስቱ ባሕ ርያተ ነፍስ በመባል በሁለት መደብ ይመደባሉ። አራቱ ባሕርያተ ሥጋ የተባሉትም መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስና እሳት ሲሆኑ ሦስቱ ባሕ ርያተ ነፍስ ደግሞ ለባዊነት፣/ዐዋቂነት/ ነባቢነት፣ /ተናጋሪነት/ ሕ ያውነት በመባል ይታወቃሉ። «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።» ዘፍ ፪፥፯ የሚለው ቃል ሰው ከላይ በዝርዝር የተፃፉትን አሟልቶ መፈጠሩን ያጠይቃል።

ከዚህም በተጓዳኝ አዳም መልኩም እጅግ ውብ ነበር። «ወይፈደፍድ ብርሃኑ ለአዳም እምብርሃነ ፀሐይ ወይበርህ ሥጋሁ ከመ ኮከበ ጽባሕ እንዲል» /ቀሌም/። የአዳም ብርሃን ከፀሐይ ብርሃን ይልቅ ይበልጣል ሥጋውም እንደ አጥቢያ ኮከብ ያበራል የሰውን ልጅ አፈጣጠር ለማወቅ አጠቃላይ ሥነ-ፍጥርት/የአዳም ብርሃን ከፀሐይ ብርሃን ይልቅ ይበልጣል ሥጋውም እንደ አጥቢያ ኮከብ ያበራል። የተፈጠረበትን መንገድ በአጭሩ ለማየት ግድ ይላል። እግዚአብሔር ሥነ-ፍጥረትን እምኀበ አልቦ ኀቡ-ቦ /ካለመኖር ወደ መኖር/ ከኢምንት ወደ ምንት አምጥቶ ያለገኛቸውም ሆነ ከተፈጠሩት ላይ የፈጠራቸው ፍጥረታት ያስገኘው በሦስት መንገድ ነው። እነርሱም፦

፩. በሐልዮ ማለት በማሰብ ነው። ይኸውም እግዚአብሔር ሊሠራው ሊፈጥረው የወደደውን ፍጥረታት በአንደበቱ ቃል ሳይናገር በኅሊናው ብቻ አስቦ በመፍቀዱ የፈጠራቸው ናቸው። «በመጀመሪያ እግዚአብሐ

ጸግነት ሲገልጽ «ጌታ የሁሉ ጌታ ነው ለሚጠሩትም ሁሉ ባዕለጸጋ ነው።» ሮሜ ፲:፲፪ ብሏል።

ሌላው መሬት ታጋሽ ናት። ቢያርሷት፣ ቢቆፍሯት፣ ቆሻሻ ቢደፉባት፣ ቢቀብሩባት፣ ለምን አትልም። ጻድቁንም ኃጥኡንም ሁሉን እንደ ጠባዩ እንደምግባሩ ችላ ትኖራለች። እግዚአብሔርም ታጋሽና ቻይ ነው። የፍጥረቱን ሁሉ ክፋት ኃጢአት ችሎ ታግሶ ይኖራል። ኃይል ሳለው እንደሌለው ሆኖ ይታያል። እያየ እንዳላየ፣ እየሰማ እንዳልሰማ፣ እያወቀ እንዳላወቀ ሆኖ ያልፋልና። «ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።» ሮሜ ፩:፲፮ ይህ ታጋሽነቱ ከመሬት ባሕርይ ጋር ያመሳስለዋል። ሰውም የመሬት ባሕርይ እንዳለው «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው» ዘፍ ፪:፯ በማለቱ ይታወቃል።

፪. ውኃ ሰው በታመመና ከባድ ሸክም በተሸከመ ቁጥር ከሰውነቱ ላብ ይወጣል። ይህ ላብ ሰው ከውኃ ባሕርያት መፈጠሩን ያጠይቃል። ውኃ የልዑል እግዚአብሔርን ርኅራኄና ቸርነት ይገልጣል። ውኃ ያደፈውን ሁሉ ያነጣል፣ ያጠራል፣ የተጠማውን ያረካል። ሰውም በኃጢአት ምክንያት ሕገ እግዚአብሔርን ተላልፎ ሲኖር በኋላ ተጸጽቶ ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔርም በባሕርይው ባለች ርኅራኄና ቸርነት ከኃጢአቱ ከርኩሰቱ ያነጣዋል፣ ያጠራዋል። እግዚአብሔር «ወደእኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጪ አላወጣውም።» ብሏል ዮሐ ፮:፴፯ «ከክፉ ኅሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ።» ዕብ ፲:፳፪ ተብለናልና።

ከዚህም ሌላ ውኃ ለፍጥረት ሁሉ ሕይወት ነው። «የእግዚ. አብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፎአልና።» ዘፍ ፩:፪ በውኃ ላይ





የሰፈፈው የእግዚአብሔር መንፈስ ለፍጥረቱ ሕይወትን ሰጥቶአል፣ ይሰጣልም። ሕይወት ለማግኘትም ሆነ የእግዚአብሔርን መንግስት ለመውረስ ውኃ ትልቅ ድርሻ አለው። «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም።» ዮሐ፫:፭ በማለት እግዚአብሔር ተናግሯል። ይህም በጥምቀት የሚገኝ ድኅነት ነው።

፫. ነፋስ ነፋስ የእግዚአብሔርን ፈታሒነት /ፈራጅነት/ ያሳያል። «እግዚአብሔር እስከ ምድር ዳርቻ ይፈርዳል።» ፩ሳሙ ፪:፲ በዚህ ፍርዱም ሃይማኖት ይዘው ምግባር ሠርተው በንስሐ ሕይወት በቤቱ ጸንተው የኖሩ ጻድቃንን፤ በሃይማኖት ሳይኖሩ ምግባር ሳይሠሩ የንስሐ ሕይወትን በመጥላት ከቤቱ የወጡ ኃጥአንን በባሕርይው ባለች ፈራጅነቱ ይለያል። «በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርስ ይለያቸዋል።» ማቴ፳፭:፴፪ ነፋስም እንዲሁ ፍሬውን ከገለባው ይለያልና።

ኃጥአን በደል ፈጽመው ኃጢአት ሠርተው እግዚአብሔርን ባስቆጡት ጊዜ ጻድቃንን አብሮ አያጠፋቸውም። በፈራጅነቱ ለጻድቃን ፈርዶ ይታደጋቸዋል። ኖኅን ከሰብዓ ትካት ሎጥን ከሰዶማዊያን ለይቶ እንዳዳነ ማለት ነው። «መንሹ በእጁ ነው። አውድማውን ፈጽሞ ያጠ ራል ስንዴውንም በጐታ፣ በጐተራ ይከታል ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።» ማቴ ፫:፲፪

፬. እሳት የእግዚአብሔርን ከሃሊነትን /ሁሉን ቻይነትን/ ያስረዳል። «ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ አሳብህንም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።» ኢዮብ ፵፪:፪ ተብሎ የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ተገልጧል። እሳት ሲቀጣጠል ባህር፣ ገደል ካልከለከለው በቀር ርጥቡን ደረቁን ያቃጥላል። እግዚአብሔርም በባሕርይው ያለች

ቊርነቱና ርኅራኄው ካልከለከለችው በቀር ሁሉንም ሳጥፋ ቢል ይችላል። የሚሳነው ነገር የለም። «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና።» ዘዳ ፬:፳፬ , ዕብ ፲፪:፳፱

በአጠቃላይ ሲታይ እነዚህ አራቱ ባሕርያት በሰው ሕይወት መኖራቸው የሚታወቀው የበሉትን የጠጡትን መሬት ይሸክማል ውኃ ያረጥባል፣ እሳት እንደገና ያበስላል፣ ነፋስ ጥሩ ጥሩውን ወደ ደም በማቀበሉ ይታወቃል። ከላይ በተጠቀሱት አራቱ ባሕርያተ ሥጋ ሰው እግዚአብሔርን እንደሚመስለው ሁሉ እንዲሁም ሕያው በሆነች ባሕርይ ነፍሱም ፈጣሪዋ እግዚአብሔርን ትመስላለች። የነፍስ ባሕርያት የሚባሉት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

፩. ለባዊነት   በአብ ይመስላል። ልብ ለሰው ልጅ ሕይወት መሠረታዊ ነገር ነው። ሰው በልቡ እንደሚያስብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ልባቸው አብ ነው። «አብ እንደነገረኝ እንዲሁ እናገራለሁ» ዮሐ ፲፪:፶ እንዲል። ይህን ማለቱ ከአብ ከኀልውናው ያገኘሁትን አስተምራለሁ ማለቱ ነው። ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአብ ልብነት ያስባሉ። ሰውም የሚያስብበት ልቡ በአብ ይመስላል። መስሎ ማስተማር ልማደ መጽሐፍ ነው። «ክቀድሞ ጀምሮ ያለውን ተምሳሊት እናገራለሁ» መዝ ፸፯:፪ ተብሏልና።

፪. ነባቢነት   በወልድ ይመለላል። የሰው ልጅ ነባቢ /ተናጋሪ/ እንዲሆን ሁሉ የአብና የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ወልድ /ኢየሱስ ክርስቶስ/ ነው። በወልድ ቃልነት ይናገራሉ። «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና በዐሥርቱ ቃላት በምሳሌ እንበለ ምሳሌ፥ በብዙ ኅብረ አምሳል ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዘመናትን በፈጠረበት ልጁ በዚህ ዘመን





መጨረሻ ለእኛ ተናገረ።» ዘኁ ፲፪:፮-፰ , ዕብ ፩:፩-፪

የሰው ልጅ የሚናገርበት ቃል አለው። የሰው ልጅ ቃልና የወልድ /የኢየሱስ ክርስቶስ/ ቃል የሚለይበት ነጥብ ግን አለ። የሰው ልጅ ቃል ዝርው ሲሆን ቃል የተባለ ወልድ ግን አካላዊ መሆኑ ነው። «በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ዮሐ ፩:፩ ይላልና። ከዚህም ሌላ የሰውን ፍጡርነት የወልድን ፈጣሪነት ሳንዘነጋ ነው።

፫. ሕያውነት   በመንፈስ ቅዱስ ይመስላል። «ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ።» ኢዮብ ፴፫:፬ የሰው ልጅም ሕያውነት ያለው ፍጡር ነው። ስለዚህ ሰው ስምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ ነው። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ቢሆኑም በመለኮት በሥልጣንና በአገዛዝ በባሕርይ አንድ አምላክ ይባላሉ። «እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው።» ዘዳ ፮:፬, ማቴ ፳፰:፲፱

ሰውም ለባዊነት፣ ነባቢነት፣ ሕያውነትን አጣምራ የያዘች ነፍስ ቢኖረውም አንድ ሰው ይባላል እንጂ ሦስት ሰው እንደማይባል ሁሉ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ መፈጠሩን ከላይ በዝርዝር በተገለጠው መንገድ ቢሆንም ቅሉ በእግዚአብሔር ባሕርይ ብቻ እንጂ በሰው ልጅ ባሕርይ በፍጹምነት የማይገኙትን መሠረታዊ ነገሮች ሳንዘነጋ ነው። እነርሱም ሁሉን ቻይነት፣ አለመለወጥ፣ አለመወሰን /ሁሉም ቦታ የሚገኝ/፣ አለመከፋፈል፣ ቅንፍርድ፣ ሁሉን ማወቅ፣ እውነተኛ ፍቅር ናቸው። እነዚህ በሰው ልጅ ባሕርይ በፍጹምነት እንደ እግዚአብሔር አይገኙምና።

አዳም ሲፈጠር የሠላሳ ዓመት ጐልማሳ ነበር። ቁመቱ እጅግ ሳይረዝም በጣምም ሳያጥር መካከለኛ፣ መልኩም እጅግ ያማረ ነበር።

አዳም ማለት ያማረ ማለት ነውና። አዳምን እግዚአብሔር ድካም፣ እንቅልፍ፣ መንቃት እንዲስማማ አድርጐ ፈጠረው። ድካምና እንቅልፍ የሥጋ፣ መንቃትና መትጋት የነፍስ ግብር ናቸው። «አንተ የምትተኛ ንቃ።» ኤፌ ፭:፲፬ ይህ ቃል ለሥጋና ለነፍስ የተነገረ ቢሆንም የቃሉ ትርጉም ግን የኃጢአት እንቅልፍ ይዞህ የተኛህ በንስሐ ሕይወት ንቃ ማለቱ ነው።

እንዲሁም ሰውን የሚቆም ሰማያዊ፥ የሚቀመጥ ምድራዊ፥ የሚተኛ መዋቲ፥ የሚነቃ /የሚነሣ/ ትንሣኤ ያለው አድርጐ ፈጥሮታል። አዳም በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ኤልዳ በተባለች ቦታ ከተፈጠረ በኋላ አርባ ቀን በመላእክት ተጠብቋል። በአርባኛው ቀን ቅዱሳን መላእክት የብርሃን ልብስ አጐናጽፈው፥ የብርሃን ዘውድ አቀዳጅተው፥ የብርሃን በትር አስይዘው፥ በብርሃን ሠረገላ አስቀምጠው ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘፈጠሮ ለአዳም እያሉ በዕለተ ዓርብ በሦስት ሰዓት ወደ ገነት አስገቡት። ኩፋሌ ፬:፱

፫. የሰው ልጅ ጥንት በገነት

እግዚአብሔር ገነትን ጥንት ለሰዉ ልጅ አስቀድሞ ያዘጋጃት ቦታ ናት። «እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ የኤደን ገነትን ተከለ። የፈጠረውንም ሰው በዚያው አኖረው።» ዘፍ ፪:፰ አዳም እግዚአብሔር በፈጠረለትና በፈቀደለት ገነት ሲኖር ሕይወት ምን ይመስል ነበር? የፈጠረው አምላክ በባሕርይው ፍጹም ስለሆነ የእጁ ሥራ የሆነውን ሰው ፍጹም አድርጐ ፈጥሮታል። «ሥራው ፍጹም ነው።» ዘዳ ፴፪:፬ ይላልና። የሰው ፈጣሪ አግዚአብሔር በባሕርይው ፍጹም መሆኑም «የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ» በሚለው ቃልይታወቃል። ማቴ ፭:፵፰ ስለዚህ የሰው ልጅ ጥንት በገነት ሲኖር የሚከተሉት ባሕርያት ነበሩት።





ሀ/ ፍጹም ነበረ፥ ፍጹም ማለት ሙሉ የሆነና ጉድለት የሌለበት የሚል ትርጉም አለው። ሰውን እግዚአብሔር ከሰባት ግብራት የፈጠረው ስለሆነ ፍጹም ነበር። ሰባት ቁጥር በዕብራውያን ፍጹም ነውና። «እስመ ኍልቈ ሳብዕ በኀበ ዕብራውያን ፍጹም ውእቱ» እንዲል በዕብራውያን ዘንድ ሰባት ቁጥር ፍጹም ነው። ልበ አምላክ ንጉሥ ዳዊትም «ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለው» መዝ ፻፴፰:፲፬ ያለው ሰው ቀድሞ ሲፈጠር ፍጹም ስለሆነ ነው።

ለ/ ቅዱስ ነበረ፥ ቅዱስ የሚለው ቃል "ቀደሰ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ አመሰገነ፣ ለየ፣ መረጠ፣ አከበረ ማለት ነው። ቅድስና ደግሞ የባሕርይና የጸጋ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። የባሕርይ ቅድስና ገንዘብነቱ ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህን ቅድስና ራሱ ሲናገር «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝ» ዘሌ ፲፱:፪ ብሏል። በባሕርይው ቅዱስ የሆነ እግዚአብሔር አዳምን በጸጋ ቅዱስ አድርጐ ፈጥሮታል።

አዳም ቅዱስ ተብሎ የሚጠራውም የእግዚአብሔር መቅደስ በመሆኑና የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጡ ስላደረ ነው። ፩ቆሮ ፫:፲፮ እኔ ቅዱስ ነኝ ያለ እግዚአብሔር የእጁ ሥራ ሰውን «ቅዱሳን ሁኑ»አለ። ፩ጴጥ.፩፥፲፮

ሐ/ ክቡር ነበር፥ ቃሉ ጌትነት፣ ከፍተኛ ማዕረግ ያለው መሆኑን ይገልጣል። አዳም በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረ ክቡር ሰው ነው። «የአግዚአብሔር ምሳሌና ክቡር ስለሆነ» ፩ቆሮ ፲፩:፯ ይለዋልና። በቅድስና ተፈጥሮ ቅድስናን ገንዘብ አድርጐ እንደ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን እያመሰገነ በገነት ይኖር ነበር። አዳም ፍጥረታት በሙሉ ክቡር ይሉት ነበር። «እግዚአብሔርም የቀደሰውን ክቡር ብትለው ትከብራለህ።» ኢሳ ፶፰:፲፫ እንዲል።

ሐዋርያው «ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል» ፪ጴጥ፪:፲፱ አለ። ስለዚህ በጥፋት ባሪያዎች /በዲያብሎስ የግብር ልጆች/ እንዳንወሰድ ሐዋርያው «አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር ከማን እንደተማርኸው ታውቃለህና ከሕፃንነትህም ጀምረህ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃልና» ፪ጢሞ፫:፲፬-፲፭ብሏል።

ጥበብ፣ ድኅነት፣ ሕይወት ከሚሰጡ ቅዱሳት መጻሕፍት አንዱ በሆነው ድርሳነ ሚካኤል ዘሰኔ ላይ እንደተፃፈው ወደ ቅድስት አፎሚያ ጠላት የቀረበው የብርሃን መልአክ በመምሰል ራሱን ለውጦ ነበር። እርሷ ግን አልተሸነፈችም። «በእምነት ጸንታ ተቃወመችው።» ፩ጴጥ፭:፱ ስለዚህ ሐዋርያው ለክርስቲያኖች «የጸኑትን አስቡ» ዕብ፲፪:፬ ከማለቱም ባሻገር «የኑሮአቸውን ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው» ዕብ፲፫:፯ አለ።

ለ/ ደካማ ጎናቸውን በመጠቀም

ሰይጣን ሰውን የሚፈታተነው ብዙውን ጊዜ ደካማ ጎኑን በማጥናት ከኛ የበለጠ ለኛ ያዘነ የተቆረቆረ፣ ያሰበ በመምሰል ሥጋዊ ምኞትን በልቡናው በማሳደር ነው። ለአዳም አምላክ መሆንህን ስለማይወድ ነው እትብላ ያለህ ብሎታል። ብትበላ ግን ፈጣሪ ትሆናለህ አለው። «እንደ እግዚእብሔር መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።» ዘፍ ፫:፭ አለ።

በኪሩቤል ዙፋን ላይ ተቀምጠህ እምላክ ሰማይ ወምድር መሆንህን ስለማይፈልግ ነው አለው። አዳም የጸጋ አምላክ ስለነበረ የባሕርይ አምላክ መሆንን ተመኘ። ሐዋርያው «ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም» ያለው ለዚህ ነው። ያዕ. ፬:፪ ያለው ለዚህ ነው። ዛሬም





የጐደለንን ሥጋዊ ፍላጐት በማጥናት የሰይጣን የግብር ልጆች በሥጋዊ ምኞት እንዳይፈትኑን አንጠንቀቅ። «ተጠንቀቁ» ማቴ ፳፬:፬ ተብሏልና።

ሐ/ ቃለ እግዚአብሔርን በማጣመም

ሰይጣንና የግብር ልጆቹ ከሚታወቁበት አንዱ መንገድ ይህ ነው። እባብ በልሳነ ሰብዕ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዟልን በማለት ለአዳም ተናገረ። እግዚአብሔር ግን ለአዳም ሁሉን አልከለከለውም። «ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ» ዘፍ፪:፲፯ ብሎታልና። እግዚአብሔርም፣ መምህራንም ፣ቅዱሳት መጻሕፍትም ፣ያላሉትን እያጣመሙ እውነቱን በሐሰት ብርሃኑን በጨለማ ጽድቁን በኩነኔ እየለወጡ የዲያብሎስ የግብር ልጆች ቃለ እግዚአብሔርን ያጣምማሉ።

እንደዚህ ያሉትን እኩያን ሐዋርያው ሲያወግዝ «የሚያናውጧችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።» ገላ፩:፯ አለ። ስለእውነተኞቹ መምህራንም ሲመሰክር «የእግዚእብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎች አይደለንምና በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን።» ፪ቆሮ ፪:፲፯ ብሏል።

ሐዋርያው የሃይማኖት ሰዎች ከሰይጣን የግብር ልጆች እንዲጠበቁ ሲያስተምር «እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትና ማሰናከያ የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ። ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና።» ሮሜ፲፮ :፲፯-፲፰ አለ።

ለ/ የሥጋ ሞት ይህም መጠሪያው ይለያያል:: ይኸውም እንደሚከተለው ይገለፃል::

* እንቅልፍ ይባላል:: የሚተኛ ሰው ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ነፍሱ ከሥጋው የተለየችበት ሰውም በትንሣኤ ዘጉባኤ ይነሣልና ሞትን እንቅልፍ አለው:: «ዳዊትም ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ በዳዊት ከተማም ተቀበረ::»፩ነገ፪:፲ ስለ ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ አሟሟትም ሐዋርያው ሲገልጽ «ተንበርክኮም ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ:: ይህንም ብሎ አንቀላፋ::» ሐዋ፯:፷ ብሏል:: ቅዱስ ጳውሎስም «ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ /እንደአሕዛብ/ እንዳታዝኑ አንቀላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን::» በማለት ተስፋ ትንሣኤ ሙታንን አስተምሯል::፩ተሰ ፬:፲፫

* መንገድ ይባላል:: «ዳዊትም የሚሞትበት ቀን ደረሰ:: ልጁንም ሰሎሞንን እንዲህ ሲል አዘዘው እኔ የምድር ሁሉ መንገድ እሄዳለሁ በርታ ሰው ሁን» ብሎታል:: ፩ነገ. ፪:፩-፪ ይህን ቀጥተኛ መንገድ ለመሄድ ሰው ሁኖ መገኘት ግድ ይላል:: «ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና::» ፊል፩:፳፫ በማለት ሐዋርያውም ሞት መንገድ መሆኑን ገልጧል::

* ስንብት ይባላል:: ጌታን በክንዱ ያቀፈው አረጋዊው ስምዖን «ጌታ ሆይ እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና» ሉቃ ፪:፳፱ በማለት ስንብት መሆኑን ተናገሯል::

ሐ/ የዘላለም ሞት /ሁለተኛ ሞት/ ይባላል:: ይህን ሐዋርያው በራእይ መጽሐፉ እንዲህ ይገልጠዋል:: «ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍስ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኞችም ጣዖትንም





የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው:: ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው::» ብሏል:: ራእ፳ ፩:፰ ይህ ዓይነት ሞት ደግሞ በሰዎች ላይ የሚደርሰው ሰዎች ከሃይማኖት ይልቅ ክህደትን ከጽድቅ ይልቅ ኃጢአትን ገንዘብ ሲያደርጉ ነው:: «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና::» ሮሜ ፮:፳፫

ሰይጣን ሞትን አትሞቱም ብሎ በመዋሸት የሰውን ልጅ ለዚህ ለሁለተኛው ሞት መረቡን ዘርግቶለት ነበር:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዳም በገባው ቃል ኪዳን መሠረት የጠላት መረቡን በጥሶበታል:: ዕቅዱን አፍርሶበታል:: «ከሲዖል እጅ እታደጋቸዋለሁ ከሞትም እቤዣቸዋለሁ» ሆሴ ፲፫:፲፬ በማለት በነቢያት ያናገረውን ትንቢት በአካለ ነፍስ ሲዖል ወርዶ ሰውን ነፃ አወጣ:: ድልን ለሰው ልጆች አቀዳጀ:: ፩ቆሮ ፲፭: ፶፭-፶፯, ፩ጴጥ፫:፲፱-፳

ሠ/ ከዕፀዋት ሁሉ ዕፀ በለስን /ዛፍ/ በማሳየት

እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው መልአካዊ ባሕርይና እንስሳዊ ባሕርይ እንዲኖረው አድርጎ ነው:: ይህም ማለት በመልአካዊ ባሕ ርይው ይጾማል፣ ይጸልያል፣ ይዘምራል፣ ይቀድሳል፣ ያመሰግናል:: «ወበእንተዝ ፈጠሮ ለሰብእ ከመ ይትለአኮ በአምሳለ መላእክት»ስለዚህ በመላእክት አምሳል ይላከው ዘንድ ሰውን ፈጠረ:: እንዲል በእንስሳዊ ባሕርይው ደግሞ ከዚህ የተለየ ነው ይራባል፣ ይጠማል፣ ይደክማል ስለዚህ ምግበ ሥጋ አስፈላጊው ነው:: «ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቅ ዛፍ አትብላ» ዘፍ፪:፲፯ ብሎታል:: በዚህ ገጸ ንባብ ብላ ያለ እምላክ አትብላ ሲል አዳምን አዞታል::

እግዚአብሔር በገነት የተከላቸው ሦስት ዓይነት ዕፀዋት እንደሆኑ መጻሕፍት ያስረዳሉ:: እነርሱም

፩. ለማየት ደስ የሚያሰኝ ለመብላት መልካም የሆነ ዛፍ

፪. በገነት መካከል የሕይወት ዛፍ

፫. መልካምና ክፉን የሚያስታውቀውን ዛፍ አበቀለ። ዘፍ ፪:፱

ከእነዚህ ሦስቱ ዕጽዋት ውስጥ የሕይወት ዛፍን ብላም አትብላም አላለውም። መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውን ዕፀ በለስን ግን አትብላ በማለት አዞታል። አዳም ዕፀ በለስን ባይበላ እንዲበላ የተፈቀደለት ለማየት ደስ የሚያሰኝ ለመብላት መልካም የሆነ ዛፍ ነበር።

አዳም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ለልጥኖበት ከእግዚ አብሔር እንዳይጣላ የሚያስፈልገውን ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ አዘጋጅቶለታል። ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያጣው የሥጋ ምኞት የዓይን አምሮት ሲገዛው ነው። ፩ዮሐ፪:፲፮ ዲያብሎስ ይህን ስለሚያውቅ ዕፀ በለስን ለአዳም በማሳየት ከእግዚአብሔር ለየው።

እግዚአብሔር ክፉና ደጉን የምታስታውቀውን ዛፍ በኤደን ገነት ተከለ። ከርሷም እንዳይበሉ ከለከላቸው። ይህም ማለት ክፉ ምን እንደሆነ ደግ ምን እንደሆነ ለይተው በማወቅ ታዛዥነታቸውን ያሳዩ ዘንድ ነው። አግዚአብሔርን መታዘዝ መልካምና ሕይወት ነው። ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ደግሞ ክፉ የሆነና ሞት ነው። እግዚ አብሔር ሰውን በክፉ ባይፈትንም ሰዎች ክፉን ለማድረግ መረጡ። ያዕ ፩:፲፫ «ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች። ከፍሬውም ወለደችና በላች ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው። እርሱም ከርስዋ ጋር በላ። እነርሱም ራ ቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ።» ዘፍ ፫:፮

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው ኅብረት ተቃወሰ። ሰውም ከእግዚአብሔር ፊት ሸሸ ቅጠል ውስጥ ተሸሸገ ለእርቃኑ መሸፈኛ ቅጠ





ል ቆርጦ አገለደመ። ከጥፋት በኋላ ለሰው ከእግዚአብሔር ፊት መቅረብ የተሻለ መስሎ አልታየውም። ፈራ፣ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ፣ ልቡ በፍርሃት ቀለጠበትና ሣሩን ቅጠሉን ዛፉ ተራራውን ከእግዚአብሔር ቁጣ መደበቂያ ለማድረግ ሞከረ። ካለመታዘዝ የተነሣ በኀሊና ወቀሳ የሚጨነቅ ሆነ። «ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጣላልና፣ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም።» ዮሐ ፫:፳ እንዲል

በሰውና ሰው መካከል የነበረው አንድነትም ፈረሰ። አንደኛው ራሱን ለማጽደቅ ሲል ሌላውን ጥፋተኛ አድርጎ ማቅረቡ ግድ ሆነበት። አዳም በበኩሉ ራሱን ነፃ ለማድረግ ሲል 'ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠ ኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ በማለት ሔዋንን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ጭምር በጥፋተኝነት ፈረጀ። ዘፍ፫:፲፪ ሔዋንም በበኩሏ በእባብ አመካኘች። ሁለቱም ራሳቸውን ነፃ ለማድረግ ከንቱ ሙከራ አደረጉ። ሥቃይ፣ ጭንቀት፣ ሽብር... ኃጢአትን ተከትለው መጡ።

በሰው በደል ምክንያት ምድር ሁሉ ከእርግማን በታች ወደቀች ። «ምድር ካንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን።» ዘፍ ፫:፲፯ ተባለ። የዚህ ዓለም ገዥ ሰው ራሱ ለሰይጣን ከማስገዛቱም በላይ የሚገዛውን ዓለም ይዞ በሰይጣን ቁጥጥር ሥር በመዋሉ ዓለማችን ከአዳም ጋር ለሰይጣን ተገዥ ሆነች። ከመራራ ውስጥ ጣፋጭ ነገር ከርኩስ ቅድስና መፍለቅ አይችልምና አዳም ልጆቹን በራሱ ባሕርይ አምሳል ወለደ። የአብራኩ ክፋዮች ልጆቹም ሲወለዱ ከጸጋ እግዚአብሔር የተራቆቱ ምስኪኖች ሆኑ።

፮. ከውድቀት በኋላ የሰውን ልጅ ሕይወት የታደገው ማነውላ

በባሕርይው ኅልፈት፣ በመንግሥቱ ሽረት የሌለበት እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ በልዩ ፍቅር የወደደው ሰው መሆኑ

ይታወቅ ዘንድ ሰውን በምሳሌአችን ወይም በአርአያችን እንፍጠር በማለቱና ሰውም በምክረ ከይሲ ከአምላኩ ከተለያየ በኋላ ፈልጐ እስከ ሞት ድረስ በመውደዱ ይታወቃል:: «ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም::» ዮሐ፲፭:፲፫ እንዲል:: የሰውን ልጅ ለማዳን እግዚአብሔር በልዕልና ሆኖ አራቱን ማዕዘን በእውነት ተመለከተ:: መዓዛ ንጽህና መዓዛ ቅድስና አስተባብራ የያዘች: ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ያዘጋጃትን ድንግል ማሪያምን ተመለከተ ደም ግባቷን ወደደ ሥጋዋን ለተዋሕዶ መረጠ::

የሰው ልጅ ያጣውን ጸጋ ሁሉ ያገኘው በመጀመሪያ በድንግል ማርያም በኩል ነው:: ስለዚህም ድንግል ማርያም ምክንያተ ድኅነት ትባላለች:: ንጽሓ ሥጋ፣ ንጽሓ ነፍስ፣ ንጽሓ ልቡና አስተባብራ የተገኘችው ድንግል ማሪያም ጌታን ወለደች:: በጌታችን መወለድ፣ መጠመቅ፣ ሞትና ትንሣኤ የሰው ልጅ ቀድሞ ወደ ነበረበት ክብሩ ተመለሰ: ያጣውን ሁሉ አገኘ:: በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ አዳም በፈ ጸመው በደልና በሰራው ኃጢአት እርሱና ልጆቹ የሰይጣን ተገዥ በመሆናቸው የእግዚአብሔር ልጆች በመባል ፈንታ የዲያብሎስ ልጆች፣ የእባብ የአፉኝት ልጆች ተባሉ::ማቴ፫:፯,፲፪:፴፬ ታዲያ ይህን ስማቸውንና ግብራቸውን የቀየረላቸውን ያዳናቸው ጸጋቸውን የመለሰላቸው ማነው?

### ሀ/ ነቢይ ነውን?

ነቢይ ማለት ቃልን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለሕዝብ የሚናገር የእግዚአብሔር ሰው ፩ሳሙ ፱:፮፦ ባለራእይ ፩ሳሙ ፱:፱፦ የእግዚ አብሔር ባሪያ ፪ነገ፳፬:፪፦ ቃሉን በብዙ ዓይነት መንገድ የተናገረ ዕብ ፩:፩ ነቢይ ይባላል:: ከጌታችን ልደት አስቀድሞ ዓበይት ነቢያት ደቂቀ ነቢያትና መጽሐፍ ያልተጻፈላቸው ሌሎች የቃል ነቢያት





ተነስተው አልፈዋል:: ነገር ግን አንዳቸውም አዳምን ለማዳን አልቻሉም:: «ወንድም ወንድሙን አያድንም ሰውም አያድንም::» መዝ ፵፰:፯

ለምን ቢባል እነርሱ ራሳቸው የውርስ ኃጢአት /ጥንተ አብሶ/ ባለዕዳዎች ስለነበሩ ነው:: «ሁላችን እንደርኩስ ሰው ሆነናል:: ጽድቃችን ሁሉ እንደ መርገመ ጨርቅ ነው::» ኢሳ ፷፬:፮ በማለት ነቢዩ እንደመሰከረ:: ባለዕዳ ለሌላ ባለዕዳ ዋስ መሆን እንደማይችል እነርሱም የኃጢአት ባለዕዳዎች ስለነበሩ ነው:: ነቢዩ ዳዊትም «እናቴ በኃጢአት ወለደችኝ» መዝ ፶:፭ ብሏል::

ይህም ማለት እናቴ ሔዋን ኃጢአትን በኃልዩ /በማሰብ/ ፀንሳ፣ በነቢብ /በመናገር/ ወልዳ፣ በገቢር /በመሥራት/ በምታሳድግበት ወራት ተወልጃለሁና ሲል ነው:: ስለዚህ ነቢያት አዳምን ሊያድኑት እንዳልቻሉ በትንቢት ተናገሩ:: ከዚህም የተነሳ አዳምን ሊያድነው የሚችል ነቢይ አይደለም:: ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስንም "ነቢዩ ኢየሱስ" ማለት ሥርየት የሌለው ኃጢአት ነው:: ነቢይነት ለርሱ ገንዘቡ ቢሆንም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት እርሱ በጸጋ ነቢይነትን ከተቀበሉ ነቢያት ተርታ አይመደብም:: የነቢያት ፈጣሪ የነቢያት አስገኝ ነውና::

### ለ/ መልአክ ነውን?

መልአክ ማለት የቃሉ ትርጉም መልዕክተኛ ማለት ነው:: አገልግሎታቸውም ዘወትር እግዚአብሔርን ማመስገን፣ ማወደስ፣ የሰው ልጆችንም በተሰጣቸው ሥልጣን መጠበቅ፣ መርዳት፣ ማማለድ ነው:: ዘፀ፳፫:፳, መዝ፴፫:፯, ዘካ፩:፲፪ ስለዚህ አዳምን ያዳነው የእግዚአብሔር መልአክ አይደለም:: ምክንያቱም ቅዱሳን መላእክት ለሰው ሥጋና

ደም ተለዋጭ የሚሆን ሥጋና ደም የላቸውምና ነው:: «ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ::» ዕብ ፪:፲፬ ተብሏልና::

ከዚህም በተጓዳኝ የሰውን ሁለንተና ባሕርይ ገንዘብ ያላደረገ አዳኝ ሊሆን ስለማይችል ነው:: «የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም::» ዕብ ፪:፲፮ በሚለት ሐዋርያው እንዳስተማረ በአዳም የሞት ፍርድ የፈረደ ከገነት ያወጣው መልአክ ስላይደለ ፍርድን ሊያነሣለትና ወደ ገነት ሊመልሰው፣ ሊያድነው አይችልም:: «መዳን በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና::» ሐዋ ፬:፲፪ እርሱም ኢየሱስ ነው:: «እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ::» ማቴ ፩:፳፩ እንዲል::

ሐ/ አምላክ ነውን?

አዎን አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: «እኮ በመልአክ ወእኮ በተንባል አላ ለሊሁ እግዚእ ይመጽእ ወያድኅነነ::» በመልአክ ወይም በመልእክተኛ ያይደለ ጌታ ራሱ መጥቶ አዳነን እንዲል:: ለምን ቢባል አዳም ሹመቱን፣ ክብሩን፣ ጸጋውን አጥቷል:: ንጉሥነቱን የጸጋ ገዠነቱ ቀርቷል:: ፍርድም ተፈርዶበታል:: አስቀድሞ እነዚህን ስጦታዎች የሰጠው በኋላም የነሳው እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህም ሊሾም ሊሽርና ሊቀድስ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው::

የመጀመሪያው ሹመቱ በእግዚአብሔር አምላክ ከተሰጠ የሁለተኛውም ሹመት በእግዚአብሔር እምላክ መሆን አለበት:: አዳምን ወደ ቀደመ ክብሩና ማንነቱ መልሶ በሐዲስ ተፈጥሮ ሊያከብረው የሚችል እግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው:: አዳም ባለዕዳ ነው:: ይህንን የሞት ዕዳ ከፍሎ ነፃ ሊያወጣውና ሞትን ሊያሸንፍ የሚችል እግዚአብሔር እምላክ ብቻ ነው ማንም ፍጡር ይህንን





ማድረግ አይችልም:: ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ፈጽሟልና አዳኝ አምላክ ነው:: ከዚህም የተነሣ ጌታችን ለአዳም መዳንን ብቻ ሳይሆን ሞትን የማሸነፍ ስልጣን ሰጥቶታል:: ሞትን በሞቱ ድል አድርጐለታልና:: ፩ቆሮ ፲፭:፶፭

ኢየሱስ ክርስቶስ የራቀውን አዳምን በፍቅሩ አቅርቧል:: ወደ አዳም የቀረበ ኃጢአትንም አርቋል:: ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሐር ክንድ ይባላል:: «ክንዴ መድኃኒት አመጣልኝ»ኢሳ ፶፯:፲፱ በክንድ የራቀን ማቅረብ የቀረበን ማራቅ እንደሚቻል:: ኃጢአት በኢየሱስ ክርስቶስ ከአዳም ርቋል:: አዳም ወደ እግዚአብሔር ቀርቧል:: አዳምና ሔዋን የተዘጋባቸውን ገነት ከፍቶ ማስገባት የቻለ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው:: የተዘጋ የሚከፍት አምላክ ብቻ ነው:: «የዳዊትም ቤት መክፈቻ በጫንቃው ላይ ነው:: እርሱም ይከፍታል የሚዘጋ የለም እርሱም ይዘጋል የሚከፍት የለም::» ኢሳ ፳፪:፳፪ እንዲል::

እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥረው በመለኮቱ /በአምላክነቱ/ ዐውቀው ሥጋና መለኮት እርስ በርሳቸው ባዕዳን ነበሩ:: ሲያድነው ግን የመለኮትን ገንዘብ ለሥጋ፣ የሥጋን ገንዘብ ለመለኮት /ከኃጢአት በስተቀር/ አንድ አደረገ:: ዕብ፪:፲፯ መለኮትና ሥጋ ተዛመዱ:: በተዋሕዶ አንድ ሆኑ:: «ቃልም ሥጋ ሆነ» ዮሐ ፩:፲፬ ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ እዳምን ያዳነው በተዋሕዶ ነው:: ሞት ከኛ ጋር ተዋሕዶ ይኖር ነበርና ሞትን ይሽረው ዘንድ መለኮት ከኛ ሥጋ ጋር ተዋሐደ::

እንዲሁም ዲያብሎስ በእባብ ተሰውሮ /ተዋሕዶ/ አዳምና ሔዋንን አስቷቸው ነበርና መለኮትም በሰው ሥጋ ተሰውሮ / ተዋሕዶ/ ዲያብሎስን ድል ነሳው:: ቆላ፪:፲፬ ለምን ቢሉ ምስጢርን በምስጢር መመለስና መሻር የእግዚአብሔር ጥበቡ ነውና:: ስለዚህ ኢየሱስ

አብሔር ነኝ» ኢሳ ፵፰:፲፯ ብሏል። እግዚአብሔር በራሱ ወገኖቹን እንዳስተማረ ሁሉ በሐዋርያትም፣ በሊቃውንትም፣ በካህናትም አድሮ አስተምሯል። ከእነርሱም ጠይቆ መረዳት እንደሚገባ «አባትህን ጠይቅ ያስታውቅህማል፣ ካህናትን ጠይቅ ይነግሩህማል» ዘዳ ፴፪:፯ ተብሏል። እንዲሁም እኛ «የትናንት ብቻ ነን ምንም አናውቅም ስለዚህ የቀደመውን ትውልድ ጠይቅ አባቶቻቸውም ለመረመሩት ነገር ትጋ እነርሱ የሚያስተምሩህና የሚነግሩህ ቃል ከልባቸው የሚያወጡ አይደሉምን?» ብሏል። ኢዮብ ፰:፱ ይህን ያወቀው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በአባቶቹ ትምህርት ድኅነት፣ ሕይወት ሲያገኝበት ሌላኛው ወገን ግን ይህን እውቀት በመጥላቱና በማጣቱ ጠፍቶአል።

እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረትም አድሮ ያስተምራል። እግዚአብሔር ፍጥረታትን የፈጠረው ለእንክሮ ለተዘክሮ፣ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ብቻ ያይደለ ለመማሪያም ጭምር ነው። «እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በፍጥረቱ ይታወቃል።» ሮሜ ፩:፳፩ እንዲል። ከእግዚአብሔር ፍጥረታት ውስጥ ሰው ከሚከተሉት መማር እንደሚችል መጻሕፍት ይመሰክራሉ።

### ከእንስሳ

የየዕ ምድሩ ጻድቅ «እንስሶችን ጠይቅ ያስተምሩህማል» ኢዮብ ፲፪:፯ አለ። በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ያለው ሰው በቋንቋ እንኳን ከማይግባባው ደማዊ ከሆኑ እንስሶች መማር እንደሚገባው ተናገረ። ነቢዩ ኢሳይያስም ይህንኑ ሲያስረዳ «በሬ የገዥውን አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ እስራኤል ግን አላወቀም ሕዝቤ ግን አላስተዋለም» ኢሳ ፩:፫ አለ። ይህ ቃል የጌታ ልደት ዕለት በተግባር ተፈጽሟል። «በእንግዶቹ ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው» ሉቃ ፪:፯ ትንቢቱና ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ጌታችን በቤተልሔም ሲወለድ





ከሰው ልጆች በልጠውና ቀድመው ፈጣሪያቸውን አውቀው የሚገባውን እጅ መንሻ /ትንፋሻቸውን/ ያቀረቡ እንስሶች ናቸው።

ከተጠቀሱት እንስሳት ውስጥ አህያን ብንመለከት በቃል ሰብአዊ በለዓምን አስተምራ ከእብደቱ እንዲመለስ ተናግራዋለች። ዘኁ ፳፪:፳፰ እንዲሁም «እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብ ጽ ይመጣል» ኢሳ ፲፱:፩ የተባለው ትንቢት ይፈፀም ዘንድ ጌታ ከእናቱ ጋር ወደ ግብጽ በእግዚአብሔር መልእክ አብሣሪነት ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር ሲሰደድ አህያ አብራ ተሰዳለች። ማቴ ፪:፲፫ የሆሳዕና ዕለትም ጌታዋን ለመሸከም ምድራዊ ኪሩብ ሁና ተገኝታለች። ማቴ ፳፩:፯ ስለዚህ እግዚአብሔር ከተጠቀመባቸው እንስሳዎች ውስጥ አህያ ትልቅ ሥፍራ እንዳላት ሰዎች አውቀውት ይሆን?

### ከጥቃቅን ፍጥረታት

ሀ/ ከገብረ ጉንዳን፡- ሰዎች ከገብረ ጉንዳን መማር እንደሚገባቸው ጠቢቡ ሰሎሞን ሲያስተምር «አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ መንገድዋን ተመልከተህ ጠቢብ ሁን። አለቃና አዛዥ ሳይኖራት መብልዋን በበጋ ታሰናዳለች መኖዋንም በመከር ትሰበስባች» ምሳ፮:፮-፰ አለ። ክረምት እስኪያልፍ ያለው ጊዜ አስቸጋሪ መሆኑን አውቀው ገብረ ጉንዳኖች ምግባቸውን በበጋ ይሰበስባሉ።

ምዕመናን ይህን አውቀው ፀሐይ ዕድሜያቸው ሳይጠልቅ ምግባር ትሩፋት ሊፈጽሙ ይገባል። የማይቀረው ሞት ሳይመጣ በጊዜ ንስሐ ገብተው ሥጋ ወደሙን መቀበል ይገባቸዋል። ገብረ ጉንዳን ከዚህም በተጓዳኝ በሥራ ይተጋገዛሉ። በአንድ መንገድ በሥርዓት ይጓዛሉ። ምዕመናንም በሥራ እየተጋገዙ፣ እየተረዳዱ፣ እየተደጋገፉ በሥርዓት

መኖር፣ መጓዝ እንደሚገባቸው ልብ ብለው ከገብረ ጉንዳን ሊማሩ ይገባቸዋል::

ከዚህም ሌላ ገብረ ጉንዳን የዓላማ ጽናት አላት:: አንድ ነገር ከነከሰች በኋላ ላለመልቀቅ በሚደረገው ፍልሚያ አንገቷ እስከ መቆረጥ ይደርሳል:: ይህም በዓላማ ለመጽናት አስተማሪ ነው:: «እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን የሕይወት አክሊል አቀዳጅሃለሁ» ራእ ፪:፲ ተብሏልና::

ለ/ ከሽኮኮዎች «ሽኮኮዎች ያልበረቱ ሕዝቦች ናቸው ቤታቸውን ግን በቋጥኝ ድንጋይ ውስጥ ያደርጋሉ::» ምሳ፴:፳፮ በማለት ጠቢቡ ያስተምራል:: ሽኮኮዎች ድንገት ከዓለቱ አንገታቸውን ወጣ ካደረጉ ጠላት ያጠቃቸዋል:: ክርስቲያኖችም እንዲሁ ከእግዚአብሔር ከተለዩ ጠላት ይበቀላቸዋል:: የክርስቲያኖች ዓለታቸው «እግዚአብሔር ነው:: «እግዚአብሔር ዐለቴ አምባዬ ነው::» መዝ ፲፮:፩, ፪ሳሙ ፳፪:፪ እንዲል::

ሽኮኮዎች አቅማቸውን ያውቃሉ ቤታቸውን በቋጥኝ ውስጥ ማድረጋቸው ለዚህ ነው:: ክርስቲያኖች ፈቃደ ሥጋን ለማሸነፍ የማይችሉ ደካሞች ቢሆኑም ዐለት በተባለው በክርስቶስ ቤዛነት በቤተ እግዚአብሔር ይኖራሉ:: «ያም ዐለት ክርስቶስ ነው::»፩ቆሮ፲:፬

ሐ/ ከአንበጣ፦ «አንበጣዎች ንጉሥ የላቸውም:: ሁላቸውም ግን በመልካም ሥርዓት ይሄዳሉ::» ምሳ፴:፳፯ በሥርዓት መጓዝ፣ መኖር ለክርስቲያኖች በእጅጉ ያስፈልጋል:: የምድራዊ አለቃ መኖር ያለመኖር ሕገ እግዚአብሔርን ከማክበረ እንደማያግድ ከአንበጣ ልንማር ይገባል:: ሌላው አንበጣ ክንፉ ቢነቀል መብረር አይችልም:: ምዕመናንም ያለረድኤተ እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ድርጊት መፈጸም አይችሉም:: ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም::» ዮሐ ፩:፫ ያለው ለዚህ





ነው::

ቅዱሳን ሐዋርያት እንኳ ከእርሱ ተለይተው ሌሊቱን በሙሉ በሚያውቁት ባህር ዓሣ ለማጥመድ ሞክረው አንዳች ሳያገኙ ቀርተዋል:: በኋላ ግን በቃልህ መረቡን እንጥላለን ብለው እልፍ ዓሣ አገኙ:: ዮሐ ፳፩:፮ ጌታም «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ያለው ለዚህ ነበር:: ዮሐ ፲፭:፭

መ/ ከእንሽላሊት «እንሽላሊት በእጅ ይያዛል በነገሥታት ግቢ ይኖራል::» ምሳ ፴:፳፰ ክርስቲያኖች በሥጋ ደካሞች መስለው ቢታዩም ሰዎች ድሆች ናቸው ቢሏቸውም የሚኖሩት ግን በንጉሠ ነገሥታት በእግዚአብሔር ቤት ነው:: ክርስቲያኖች በአማናዊው ቤቱ መኖር እንደሚገባቸው ጌታችን አስተምሯል:: «በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን?»ብሏልና:: ሉቃ ፪:፵፱

እንሽላሊት ጅራቷ ቢቆረጥ ተመልሶ...ይተካል:: ምዕመናንም በኃጢአት ንጽሕናቸውን ቢያጎድፉ በንስሐ ይታደሳሉ:: «እንድትጸድቅ ኃጢአትህን ተናገር» ተብሏልና:: ኢሳ፵፫:፳፮ ሐዋርያውም «ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው» ፩ጢሞ፪:፬ አለ:: በንስሐ ወደ እርሱ የሚመጡትን ጌታ በፍቅር ዓይን እየየ በደላቸውን ሳይቆጥርባቸው በደስታ ይቀበላልና:: «ወደ እኔ የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም::»ብሏልና:: ዮሐ፮:፴፯

ከሰማይ ወፎች

በዘመነ ሕገ ልቡና የነበረው የትዕግሥት አባት ኢዮብ ሲያስምር «የሰማይ ወፎችን ጠይቅ ይነግሩህማል» አለ:: ኢዮብ፲፪:፯ ጌታችንም «ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ አይዘሩም አያጭዱምም በጎታ በጎተራም አይከቱም የሰማዩ አባታቸው ይመግባቸዋል::» ብሏል:: ማቴ፮:፳፮

መክ ፫:፲፪ እንዲል::

**ለ/ ከንቱነትን**

አበቦች አብበው እንዳማሩ፣ ፍሬ እንደሰጡ፣ ሰውን እንዳስደሰቱ አይቀሩም ይረግፋሉ:: በምድር ላይ ያለ ባለሥልጣን ከሥልጣኑ እንደሚሻር፣ ሀብታሙም ደሃ እንደሚሆን፣ ኃያሉም ሰው እንደሚደከም፣ ጉበዙ ሰው እንደሚሸነፍ አበቦች ያስተምራሉ:: «ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሣር ነው:: ክብሩም ሁሉ እንደ ምድር አበባ ነው:: የእግዚ አብሔር እስትንፋስ ይነፍስበታልና ሣሩ ይደርቃል:: አበባውም ይረ ግፋል፣ በእውነት ሕዝቡ ሣር ነው::» ኢሳ ፵:፮-፯ እንዲል::

ጠቢቡ ሰሎሞንም ሰዎች ሃይማኖት ይዘው ምግባር ካልሠሩ ከንቱ መሆናቸውን ተናግሯል:: «ከንቱ፣ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው: ከፀሐይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ የሰው ትርፉ ምንድነው?» መክ ፩:፪ አለ:: ሰዎች በርትዕት ሃይማኖት ኖረው ምግባር ካልሠሩ ሕይወታቸው ከንቱ መሆኑን አውቀው ከንቱ ሥጋ፣ ከንቱ ዓለምን ድል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ከላይ ለእብነት ከጠ ቀስናቸውና ከሌሎች ሥነ ፍጥረታ ሰዎች ስለሃይማኖት ተምረው ከማወቅ ስለሰነፉ «የሰው ልጅ /ኢየሱስ ክርስቶስ/ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ ይሆንን?» ሉቃ ፲፰:፰ ተባለ::

## ፪. ያለ መሠረታዊ እውቀት ክርክር በመልመድ

ማንኛውም ክርስቲያን ስለ ርትዕት ሃይማኖት መሠረታዊ እውቀት መያዝ ይገባዋል:: መሠረታዊ እውቀት ከሌለው መልሕቋ እንደተቆረጠባት መርከብ በባሕር ላይ ወዲያና ወዲህ ይንገዋለላል:: በአንድ ቦታ ጸንቶ መቆም አይችልም:: ውኃ እንደሌላቸው ምንጮችና በዐውሎ ነፋስ እንደሚነዳ ደመና ይሆናል:: ፪ጴጥ፪:፲፯ በቃየል





መንገድ ይጓዛል:: ለበለዓም ስህተት ራሱን አሳልፎ ይሰጣል:: ይሁዳ ፩:፲፩ ስለዚህ ማንም ከከንቱ ክርክር ርቆ መሠረታዊ ሕይወት የሚሆን እውቀት መያዝ ይገባዋል:: «እውቀትንም /ጥበብን/ ገንዘብ ላደረጋት ሕይወትን ትሰጠዋለች::» መክ ፯:፲፪ ተብሏልና::

ሐዋርያው «በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቀህ የተሰጠህን አደራ /ሃይማኖትህን/ ጠ ብቅ፣ ይህ እውቀት አለን ብለው አንዳንዶች ስለእምነት ስተዋልና» ፩ጢሞ፮:፳ አለ:: ለአንድ ክርስቲያን መሠረታዊ የሃይማኖት እውቀት የሚባለው አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ነው:: «ሌሎችን ደግሞ እስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሣን ከመናገር ይልቅ እምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ::» ፩ቆሮ ፲፬:፲፱ እንዲል::

አምስቱ አዕማድ የተባሉትም ምሥጢረ ሥላሴ ፣ምሥጢረ ሥጋዌ ፣ ምሥጢረ ጥምቀት፣ ምሥጢረ ቁርባን ፣ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን ናቸው:: እነዚህ በይዘታቸው በሦስት ይመደባሉ:: ምሥጥረ ሥላሴና ምሥጢረ ሥጋዌ "ነገረ መለኮት" ሲባሉ ምሥጢረ ጥምቀትና ምሥጥረ ቁርባን "ሀብታተ ቤተክርስቲያን" ይባላሉ:: ምሥጢረ ትንሳኤ ሙታን ግን በራሱ "ነገረ ሕይወት ዘላለም" ይባላል:: «ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታንጹ እንደተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ» ቆላ ፪:፯ ተብለናል::

ስለርትዕት ሃይማኖት መሠረታዊ እውቀት ከያዝን ተቃዋሚዎችን ማሳፈር እንችላለን:: እንማርካለን እንጅ አንማረከም:: «ወደረኞቻችሁ ሁሉ ሊቃወሙና ሊከራከሩ የማይችሉትን አፍና ጥበብ እሰጣችኋለሁ» ተብሎልናልና:: ሉቃ፳፩:፲፭ መሠረታዊ እውቀት የያዘ ሰው ብርሃኑን

ከጨለማ፣ እውነቱን ከሐሰት፣ ጽድቁን ከኩነኔ ለይቶ አውቆ ማሳወቅ ይችላል እንጂ «የአምልኮ መልክ ይዞ ኃይሉን አይክድም።» ፪ጢሞ፫:፭ ይልቁንም «ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት መክሮ ተቃዋሚዎችን ይወቅሳል።» ቲቶ፩:፱

## ፫. በሥጋዊ ጥቅም በመሸነፍ

የሰማይ አዕዋፍን የሚመግብ እግዚአብሔር በአርአያውና በምሳሌው ለፈጠረው ሰውማ ምንኛ አብልጦ አብዝቶ እንደሚመግብ ባለማወቅ ብዙዎች በሥጋዊ ፍላጐት በመሸነፍ ሃይማኖታቸውን ለውጠዋል። «በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃ አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።» ገላ፭:፩ አዳምና ሔዋን በባርነት ቀንበር እንዲያዙ ያደረጋቸው ሥጋዊ ፍላጐት ነው። የባርነት ቀንበር የተባለው አንዱ በሥጋዊ ፍላጐት መሸነፍ ነው። ይኸውም ለሆድ ማደር ነው። «መብል ወዳጆች ከቶ የማይጠግቡ ውሾች ናቸው። እነርሱም ያስተውሉ ዘንድ የማይችሉ ናቸው ሁሉ ወደ መንገዳቸው ከፊተኛው እስከ ኋላኛው ድረስ ሁሉ እያንዳንዳቸው ወደ ጥቅማቸው ዘወር ብለዋል።» ኢሳ ፶፮:፲፩ ሠለበቱ ምዕት «ለምግብ ብለህ ብኩርናህን አትሽጥ» ሃይ.ዘሠለ ፳፱:፭ በማለት ያስተማሩት ለዚህ ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ ለሆዳቸው ያደሩትን ያስተውሉ ዘንድ የማይችሉ ናቸው ይላቸዋል። ጠቢቡም « ከማስተዋል መንገድ የሚሳሳት ሰው በሙታን ጉባኤ ያርፋል» አለ። ምሳ ፳፩:፮ ብዙዎች ባለማስተዋል ያለ ትክክለኛው ትርጓሜ ወደ ሆድ የገባ አያረክሰም ዝም ብላችሁ ተመገቡ አትጹሙ ብለው በሙታን ጉባኤ ሲናገሩ ይደመጣሉ፡ ለመሆኑ አዳምና ሔዋን ያረከሳቸው ምን ይሆን ወደ ሆድ የገባ መብል





አይደለምን?

በመብል የተወሰደውን ልጅነት ሊመልስ ዳግማዊ አዳም /ኢየሱስ ክርስቶስ/ ጾመ። ለሆዳቸው ያደሩ ወገኖች ግን ኢየሱስ ጾሞልናልና አንጾምም ይላሉ። ምክንያቱም የሚያመልኩት እግዚአብሔርን ሳይሆን ሆዳቸውን ነውና። «መጨረሻቸው ጥፋት ነው ሆዳቸው አምላካቸው ነው» ፊል ፫:፲፱ ተብሏል። በነቢዩ ሕዝቅኤልም «ውሸታችሁን ለሚሰሙት ሕዝቤ እየዋሻችሁ ሞት የማይገባቸውን ነፍሳት ትገድሉ ዘንድ በሕይወትም መኖር የማይገባቸውን ነፍሳት በሕይወት ታኖሩ ዘንድ ስለጭብጥ ገብስና ስለ ቁራሽ እንጀራ በሕዝቤ ዘንድ አርክሳችሁኛል።» ሕዝ ፲፫:፲፱ ይህም ማለት ስለሆዳችሁ ብላችሁ በሐሰት ትምህርታችሁ እውተኞችን ወደ ሞት ጋበዛችሁ። ሐሰተኞቹን ደግሞ እውነተኞች ናችሁ አላችሁ ማለቱ ነው።

ሌላው በገንዘብ ፍቅር መያዝ ነው። ሰይጣን ጌታን ከተፈታተነበት ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ውስጥ አንዱ ገንዘብ ነው። ዛሬም በገዳመ ቆንቶስ ድል የተነሣ ሰይጣን በገንዘብ ፍቅር ብዙዎች ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡ እያደረገ ነው። «ገንዘብ ወደው የጠፉ ሰዎች ብዙ ናቸው።» ሲራክ ፴፩:፮ ጌታችንም በመዋዕለ ስብከቱ «የሰው ሕይወቱ በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ» ሉቃ ፲፪:፲፭ ያለው የሰዎች ጥፋት ስለሚገደው ነው። በገንዘብ ፍቅር ብዙዎች ሃይማኖታቸውን መለወጣቸውን ግልጽ በሆነ ቋንቋ ሐዋርያው «ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶች ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ።» አለ።፩ጢሞ፮:፲ ከዚህም የተነሳ «አካሄዳችሁ ገንዘብ ያለ መውደድ ይሁን ያላችሁ ይብቃችሁ።» ተባለ።ዕብ፲፫:፭

## ፬. ለሥጋዊ ፍቅር /ትዳር/ ብለው

ሥጋዊያኑን አገልጋዮች በመመልከት እነርሱ እንዲህ ከሆኑ በሚል ምክንያታዊ ነገር ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ:: «ሕዝቤ ሆይ የመሩአችሁ ያስቱአችኋል የምትሄዱበትንም መንገድ ያጠፋሉ::» ኢሳ ፫:፲፪ የተባለውን ትንቢታዊ ቃል አያስተውሉም:: «ካህኑና ነቢዩ ከሚያሰክር መጠጥ የተነሣ ይበታሉ በወይን ጠጅ ይዋጣሉ::» ኢሳ፳ ፰:፯ በተባለው ትንቢታዊ ቃል መሠረት ብዙ እሰናካይ አገልጋዮች እንዳሉ የአደባባይ ምስጢር ነው::

ጽኑዓን ለነበሩ በሥጋ ድካም ለተሸነፉ አገልጋዮችም «አንተ ብዙዎችን ታስተምር ነበር:: የደከሙትን እጆች ታበረታ ነበር ቃልህ የሚሰናከለውን ያስነሣ ነበር፣ አንተም የሚብረከረከውን ጉልበት ታጸና ነበር:: አሁን ግን በአንተ ላይ መጥቶእል አንተም ደክምህ ደርሶብሃልና አንተም ተቸገርህ» ኢዮብ፬:፫-፭ ተብሎላቸዋል::

እውነተኛ አገልጋይ ራሱን የሚገዛ፣ እንደሚገባው የሚሠራ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ገር የሆነ፣ የማይከራከር፣ ገንዘብን የማይወድ፣ መሆን እንዳለበት መጻሕፍት ያስረዳሉ:: ፩ጢሞ፫:፪ ዳሩ ግን ይህን ባለማወቅ ይሁን በድፍረት አንዳንዶች አገልጋዮች ከራሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ለበጎቻቸው የማሰናከያ እንቅፋት ሆነዋል:: «ሕዝቤ የጠፉ በጎች ሆነዋል እረኞች እሳቱአቸው:» ኤር፶:፮ እንደተባለ ሐዋርያውም «አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን እታስተምርምን? እትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን? አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን? በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ የአግዚአብሔርን ሕግ ታፈርሳለህን? በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባል» ሮሜ፪:፳፩-፳፬ ያለው በሰነፎች አገልጋዮች የተነሣ የእግዚአብሔር ስም እንደሚሰደብ፣ ሰዎችም





አርቀው ባለማየትና ባለማስተዋል እነርሱን እየተመለከቱ ሃይማኖታቸውን እንደሚለውጡ ስለተመለከተ ነው::

ዘወትር ሰዎች ማየት የሚገባቸው የጸኑትን፣ በሕይወታቸው አስተማሪ የሆኑ እገልጋዮችን ነው:: ጌታችንም «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለው አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» ማቴ፭:፲፮ ያለው የአገልጋዮቹን መልካም ሥራ በማየት ሰዎች ሃይማኖታቸውን እንደሚያፀኑ ስለሚያውቅ ነው:: ለእውነተኛ አገልጋዮችም «በእውነት ሕጌ በአፉ ውስጥ ነበረች በከንፈሩም ውስጥ በደል አልተገኘበትም:: ከእኔም ጋር በሰላምና በቅንነት ሄደ ብዙ ሰዎችን ከኃጢአት መለሰ» ሚል፪:፮ ተብሎ በአምላኩ እና በእውነተኞች ክርስቲያኖች ይመሰክርለታል::

## ፮. በራስ ማስተዋል በመደገፍ

ጠቢቡ ሰሎሞን «በራስህ ማስተዋል እትደገፍ» ምሳ፫:፭ በማለት ያስተማረው በራሳቸው ማስተዋል የሚደገፉ ሰዎች እንደሚሰነካከሉና ሌሎችን እንደሚያሰናክሉ ስለሚያውቅ ነው:: በራሱ ማስተዋል የሚደገፍ ሰው ያየውን፣ የሰማውን፣ ያነበበውን በራሱ ኢምንት እውቀት እየመዘነ ይተረጉመዋል:: ይህ ደግሞ ለስህተት ይዳርጋል:: «በእነዚህ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ:: ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍትን እንዲያጣምሙ እነዚህ ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ:: እንግዲህ እናንተ ወዳጆች ሆይ ይህን አስቀድማችሁ ስለምታውቁ በዓመፀኞች ስህተት ተስባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ» ተብሏል:: ፪ጴጥ፫:፲፮-፲፯

በራሳቸው ማስተዋል የሚደግፉ ሰዎች ጣፋጩን መራራ፣ ብርሃኑን ጨለማ፣ እውነቱን ሐሰት በማለት ለራሳቸው ስተው ሌሎችን

ያስታሉ:: «እነርሱ ከዓለም ናቸው ስለዚህ ከዓለም የሆነውን ይናገራሉ ዓለሙም ይሰማቸዋል:: እኛ ግን ከእግዚአብሔር ነን እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል:: ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም::» ፩ዮሐ፬:፭

ሐዋርያው ፊልጶስ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባን «በእውኑ የምታነበውን ታስተውላለህን?» ሐዋ፰:፫ በማለት ያጠየቀው በራሱ ማስተዋል መጻሕፍትን ተርጉሞ እንዳይሳሳት ነው:: «የማያስተውል ሰው ይገለበጣል» ሆሴዕ፬:፲፬ የሚለውን የነቢይ ቃል የተረዳው ጃንደረባ የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል አለ:: ሐዋርያው ፊልጶስም በእውነት ያወቀውን የተረዳውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አንብቦ፣ ተርጉሞ አመሳጥሮ ጃንደረባውን ስላስተማረ ጃንበደረባው ተጠምቆ ሕይወትን አገኘ:: ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን መሰከረ ጃንደረባው በራሱ ማስተዋል ቢደገፍ ኖሮ ለዚህ ሕይወት በቅቶ ለወገኖቹም አይተርፍም ነበር::

በመጽሐፍ ቅዱስ «በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም እልተፈቀደም::» ጴጥ፩:፳ የተባለውን ቃል ልብ ባለማለት በራስ ማስተዋል ተደግፎ መጻሕፍትን ከመተርጐም ተርጉሞም ለስህተት ከመዳረግ መጠንቀቅ ይገባል:: "መጠየቅ ያደርጋል ሊቅ" የሚለውን መልካም ብሂል እና « በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን» ምሳ.፫+፯ የሚለውን የመጽሐፍ ቃል ይዞ ከእውነተኞቹ፣ ከመንፈሳውያኑ መምህራን ስለእውነተኛው ሃይማኖት መጠየቅ እንጂ በራስ ማስተዋል መደገፍ አይገባም:: «ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉት ነው:: ለእነርሱ የእግዚ አብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳይበራላቸው የዚህ ዓለም አምላክ /ዲያብሎስ/ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ::»





፪ቆሮ፬:፫-፬ እንዲል::

## ፰. ትንቢት መፈጸሚያ ለመሆን

ከነገደ መላእክት መሃል ሳጥናኤል፣ ከሐዋርያት መሃል ይሁዳ፣ ከሊቃውንት መሃል አርዮስ እንደተነሱ ሁሉ ከንጹሕ የስንዴ ዘር መካከል ትንቢት መፈጸሚያ ለመሆን እንክርዳዶች መብቀላቸው አይቀሬ ነው:: እንደሚነሱም ጌታ ተናግሯል:: መነሳታቸውን ብቻ ሳይሆን ብዙዎችን እንደሚያስቱ ድንቅ ምልክቶችም እንደሚያደርጉ ጭምር ተናገረ:: «ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ» አለ:: ማቴ፳፬:፳፫ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ ጌታ ይነሳሉ ያለውን ተነስተዋል ብሎ አስረግጦ ተናገረ:: «ልጆች ሆይ መጨረሻው ሰዓት ነው የክርስቶስ ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል:: ስለዚህ መጨረሻው ሰዓት እንደሆነ እናውቃለን:: ከኛ ዘንድ ወጡ ዳሩ ግን ከኛ ወገን እልነበሩም ከኛ ወገንስ ቢሆኑ ከኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር:: ነገር ግን ሁሉ ከኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ» ብሏል:: ፩ዮሐ፪:፲፰-፲፱ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ማለቱም እርሱ የባሕርይ አምላክ ሆኖ ሳለ ነቢይ፣ ፍጡር፣ አማላጅ፣ ከመላእክት እንደ አንዱ ነው ማለታቸውን ለመግለጽ ነው::

ትንቢት ስለተገነረባቸው ከኛ ወገን አልነበሩም አለ:: ከእግዚአብሔር ወገን ካልሆኑ ከማን ወገን እንደሆኑ ማስተዋል አይከብድም:: እውነተኞቹን ክርስቲያኖች ሐዋርያው «ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁ የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ»፩ጴጥ፪:፱ ብሏቸዋል:: በእውነተኛ ሃይማኖት ጸንቶ በክርስትናው መንገድ መጓዝ

ለርስቱ የተለየ ወገን ያደርጋል።

ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ቃሉን በማበተዋል ሰምቶ መተግበር ሲቻል ነው። «ንግግሬን የማታስተውሉ ቃሌን ልትሰሙ የማትችሉ እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ። የእባታችሁን ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ።» ዮሐ፰:፵፬ ብሎ ጌታ የተናገረባቸው ሰዎች የዲያብሎስ የግብር ልጆች ስለሆኑ ታቦቱን ጣዖት፣ መስቀሉን እንጨት፣ ፀበሉን ውኃ፣ እምነቱን ዐመድ፣ ክርስቶስን ነቢይ፣ እማላጅ፣ ፍጡር፣ ትንሹ እምላክ እያሉ የእባታቸውን የዲያብሎስን ድምፅ ያስተጋባሉ።

ሐዋርያው በትምህርቱ ክርስቲያኖች በዚህ የጨለማ መንገድ እንዳይጓዙ በኑፋቄ ትምህርታቸውም እንዳይወሰዱ «እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትና ማሰናከያ የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ።» ሮሜ ፲፮:፲፯ አለ። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የዲያብሎስን የግብር ልጆች ድምፅ ሰምተን በጨለማ መንገድ እየተጓዝን የምንገኝ ክርስቲያኖች «ጠላቴ ሆይ ብወድቅ እነሳለሁና በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆነኛል» ሚክ፯:፰ እያልን ዲያብሎስንና የግብር ልጆቹን ድል አድርገን በንስሐ ሕይወት ተጉዘን ለርስቱ ከተለዩ ወገኖች ጋር ልንደመር ጊዜው አሁን ነው። «ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ።» ኤፌ ፭:፲

## ፪. ድንቅ ምልክቶችን በማየት

ጌታችን በአካለ ሥጋ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረ ወቅትና በዘመነ ሐዋርያት ትምህርት ከተአምራት ጋር ስለተስማማ ጌታም ሐዋርያትም ድንቅ ምልክቶችን በማሳየት ሰዎች ትክክለኛውን





ሃይማኖት እንዲያውቁ አድርገዋል። ጌታችን «በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ።» ዮሐ ፪:፳፫ ለምሳሌ ከሐዋርያት ፊልጶስም በእውነተኛ ምልክት ብዙ ሰዎችን አሳምኗል። «ፊልጶስም ወደ ሰማሪያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው ሕዝቡም የፊልጶስም ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ የተናገረውን በአንድ ቃል አድምጠው በጌታ አመኑ።» የሐዋ ፰:፭-፯

ይህ ግን በዘመኑ ብዙዎች ወደ ክርስትናው ሃይማኖት እንዲመጡ አንዱ የማበተማሪያ መንገድ ነበር።

ክርስትና በዓለም ላይ ይህን ያህል ዘመን ካስቆጠረ በኋላ ግን ምልክትን ካላየን በስተቀር አናምንም ማለት አይሁዳዊ ጠባይ ነው። «አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ።» ፩ቆሮ፩:፳፪ ተብሏልና። አይሁድ ምልክትን አይቶ ለማመንም ይሁን ጌታን ለመፈታተን ቀርበው ምልክትን እሳየን አሉት። «እርሱ ግን መልሶ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል።» ማቴ፲፪:፴፱ በማለት ጥያቄአችሁ የክፉዎች፣ የአመንዝራዎች ጥያቄ ነው አላቸው። እሳት ከሰማይ ካላወረደ፣ በረድ ካላዘነበ፣ ሙት ካላስነሳ፣ ባሕር ካልከፈለ፣ ዕውር ካላበራ፣ ጉባጣ ካልረታ፣ ለምጻምን ካላዳነ፣ አጋንንትን ካላወጣ በስተቀር ትክክለኛ ሃይማኖት አይደለም ማለት የአመንዝራዎች ቋንቋ ነው።

ሰዎች ይህ ድርጊት ሲከናወን ቢያዩም በምትሃት መሆኑን ሳያጤኑ ይህ ነው ትክክለኛው ሃይማኖት ተአምር የሚሠራ እያሉ ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ። ሃይማኖታቸው ምንኛ እውነተኛ ቢሆን ነው ጌታ «በስሜ አጋንንት ያወጣሉ» ማር፲፮:፲፯ ያለውን በተግባር የሚያሳዩን ይላሉ። አጋንንት ከሰዎች እያወጣን ነን የሚሉ ክፍሎችም

ይህ ተግባራቸው የብቃት እየመበላቸው እጅግ ይደሰታሉ:: ጌታችን ግን «እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፣ የሚጐዳችሁም ምንም ነገር የለም:: ነገር ግን መናፍስት ስለተገዙላችሁ ደስ አይበላችሁ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለተፃፈ ደስ ይበላችሁ» ሉቃ ፲:፲፱-፳ ማለቱን አያስተውሉም::

ጌታውን አሳልፎ የሰጠ ይሁዳም አጋንንትን አውጥቶ ነበር:: ግን አልጠቀመውም:: አጋንንት የሚያወጣ ሰው ሁሉም መንፈሳዊ ዋጋ ያገኛል ማለት አይደለም:: ምክንያቱም አጋንንትን ማውጣት ከእግዚ አብሔር የሚሰጥ ጸጋ እንጂ ትሩፋት ባለመሆኑ ነው:: በጌታችን ስም ትንቢት ቢናገሩ፣ አጋንንት ቢያወጡ፣ ብዙ ድንቅ ምልክቶችን ቢ ያሳዩም እንኳን ጌታችን አላውቃችሁም ብሏቸዋልና ነው:: ማቴ ፯:፳፪ አላውቃችሁም ማለቱም ወለድኳችሁ ካድኳችሁ ማለቱ ነው:: እነዚህ ወገኖች እግዚአብሔር አላውቃችሁም ካለ የሚያውቃቸው «የዚህ ዓለም ገዥ» ዮሐ ፲፪:፴፩ ዲያብሎስ ነው «እናንተ ከአባታችሁ ከዲ ያብሎስ ናችሁ» ዮሐ ፰:፵፬ ተብለዋልና::

እግዚአብሔር ዛሬም ድንቅ ምልክትን በማየትም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች ሃይማኖታቸውን የለወጡትን ሰዎች የምሕረት እጁን ዘርግቶ ወደ እርሱ እንዲመለሱ ወደ ቤቱ እንዲገቡለት እየተጣራ ነው::«ሕዝቤ ሆይ ና ወደ ቤትህ ግባ»ኢሳ፳፮:፳ይላል::

እግዚአብሔር ወደ ቤትህ ያለው ወደ ቤተ እግዚአብሔር ማለቱ ነው:: የእግዚአብሔር ቤት የኛም ቤት ነውና ምክንያቱም እርሱ አባት እኛ ልጆቹ ነንና:: «በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንድገባ አላወቃችሁምን?» ሉቃ ፪:፵፱ እንዲል:: ጌታችንን እናቱ እና ቅዱስ ዮሴፍ ሲፈልጉት ያገኙት በቤተ መቅደሱ ነው:: እኛም ዘወትር ሰዎች ሲፈልጉን በእውነተኛው ቤተ እግዚአብሔር እንገኝ ዘንድ እርእያ





ሆነን:: «የተጠራችሁት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችኋል::» ፩ጴጥ፪:፳፩

## ፲. ሥጋዊ ሞትን በመፍራት

ሰዎች ሥጋን በመልበሳቸው እንደቅዱሳኑ የላይኛው ቤት እና ሕ ይወት ካልታያቸው ሥጋዊ ሞትን በእጅጉ ይፈራሉ:: ሐዋርያው «ልሄድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና» ፊልጵ፩:፳፫ በማለት የተናገረው የበለጠ ሕይወት መሆኑን በዓይነ ልቡናው ስለታየው ነው:: ክርስትና ስትመሠረት ልጆቿ ለአፈ አናብስት እየተጣሉ፣ በወኀኒ ቤት በእግረሙቅ ታስረው ጀርባቸው እንኪላጥ ይገረፉ፣ በሕይወት እያሉ ቆዳቸው ይገፈፍ እንደነበረ መጻሕ ፍት ይናገራሉ:: «እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ ለሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወህኒ ተፈተኑ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ» ዕብ ፲፩:፴፯ እንዲል::

ቅዱሳኑ ግን ስሰሙ የተለያዩ ጸዋተወ መከራ ሲደርስባቸው ለአፍታ እንኳን ያዘኑበት፣ የተከዙበት፣ በሕይወታቸው የተማረሩበት ጊዜ አልነበረም:: ሁሉንም በደስታ ተቀበሉት:: «ሐዋርያትም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፉአቸው በኢየሱስ ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው:: እነርሱም ስለስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ::» ሐዋ ፭:፵

ቅዱሳን ሐዋርያት ጀርባቸው እስኪላጥ ተገርፈው ደስ እንዲላቸው ያደረገው በኋላ የሚያገኙት ዋጋ እየታያቸውና የተገባላቸው ቃል ኪ ዳን ስላለ ነው:: «እውነት እላችኋለሁ እናንተ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአስራ ሁለቱ ዙፋኑ

ትቀመጣላችሁ።» ማቴ ፲፱:፳፰ ይህም ማለት ያን ጊዜስ መቀመጥ መፍረድ የለም። ዛሬ የምትፈርዱት ፍርድ የማይነቀፍባችሁ ነው ተቀባይነት አለው ማለቱ ነው። ዓለምን ድል የነሳውን አምላክ ሰላመለኩ ቅዱሳኑ ሞትን ሳይፈሩ ፈተናውን ሁሉ በድል ተወጥተዋል። «እነርሱ ክበጉ ደም የተነሳ ከምስክራቸውም ቃል የተነሳ ድል ነሱት ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም» ራእ፲፪:፲፩ ምክንያቱም «ሥጋን የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ። ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።» ማቴ፲:፳፰ የተባለው አማናዊ ቃል በልቦናችሁ ስሌዳ ስለተጻፈ ነው።

በዘመነ ሰማዕታት በክርስቲያኖች ላይ የደረሰውን መከራ ስናስታውስ የክርስትና ሃይማኖት በዓለም ላይ ይገኛል ብሎ ማሰቡ እጅግ ይከጠብዳል። ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ እውነተኞቹ ክርስቲያኖች በዘመኑ ተፈትነው ወርቅ ሃይማኖታቸውን በዓላውያን ፊት መስክረው የማይረሳ ጽናት አስተምረው የማያልፈውን ዋጋ አግኝተዋል። «በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ» ተብሎአልና። ማቴ፲:፴፪ በዘመነ ሰማዕታት በክርስቲያኖች ላይ የደረሰውን ደዋተወ መከራ በመፍራት ሃይማኖታቸውን የለወጡ ወገኖች እንዳሉ ይታወቃል። ይህ በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው መከራ በዓላውያን ነገስታት፣ በመናፍቃን ጳጳሳት ብቻ ያይደለ በጉልበት፣ በኃይል፣ በሰይፍ በተመሠረተ ሃይማኖት ጭምር እንደሆነ የታሪክ መጻሕፍት ያስረዳሉ።

በሀገራችን ኢትዮጵያም በ፱ኛው ክፍለ ዘመን የተነሳችው ዮዲት /ጉዲት/፣ በ፲፮ኛው ከፍለ ዘመን የተነሳው ግራኝ መሐመድ፣ በዓፄ ሱስንዮስ መሳሪያነት በካቶሊክ ሚሰዮናች፣ በዓፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት የእንግሊዞች ጦርነት፣ በዓፄ ዮሐንስ ፬ኛ ዘመነ መንግስት





የደርቡሽ ወራራ፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የኢጣሊያ ፋሺሽት ጦርነት፣ ብዙው ሕዝበ ክርስቲያን ሃይማኖቱን እንዲለውጥ ክማስደረጉም ባሻገር በቤተክርስቲያናችን ላይ በደረሰው ጉዳት አያሌ ብርቅና ድንቅ ቅርሶችን አውድሟል። የብዙ ክርስቲያኖችም ሕይወት ጠፍቷል።

ከሕዝበ ክርስቲያኑም በሃይማኖት የጸኑት አንገታቸው እንደ ሳም ታረደ፣ ደማቸው እንደ ጐርፍ ወረደ። የታደሉት ለሃይማኖት ሲሉ ይህን የክብር ጽዋ በአኰቴት ተቀብለው የሰማዕታትን ዋጋ አገኙ፣ የድል አክሊልን ተቀዳጁ። «እኔ ደግሞ ድል እንደነሳሁ ከአባቴም ጋር በዙፋን ላይ እንደተቀመጥሁ ድል ለነሳው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።» ራእ፫:፳፩ ተብሎ የተነገረውን ዋጋ አገኙ። በተቃራኒው መከራውን የተሳቀቁ ሥጋዊ ሞትን የፈሩ ማህተማቸውን በጠሱ ሃይማኖታቸውን ለወጡ።

ይህ በታሪክ መጻሕፍት ተጽፎ እናነበው፣ በሃይማኖት አባቶች ሲነገር እንሰማው የነበረው ሃይማኖትን በሰይፍ የመመስረትና ሰውን ገድሎ የመጽደቅ ጉዳይ በዘመናችንም በተግባር በኢሉባቡርና በጅማ በወለጋ ሲፈጸም ጽኑዓኑ የሃይማኖት አርበኞች በቤተ መቅደስ ውስጥ እያሉ እንደ ካህኑ ዘካሪያስ ደማቸው እንደ ውሃ ፈሰሰ፣ አንገታቸው ተሰየፈ፣ የሞትን ጽዋ በአኰቴት ተጐነጩት። ማቴ ፳፫:፴፭ ምዕመናኑም የአባቶቻቸውን የካህናትን አርአያ ተከተሉ። «ከእነርሱም ጋር ያሉ የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም ድል ይነሳሉ።» ራእ፲፯:፲፬ እንደተባለላቸው ሃይማኖታችንን አንለውጥም፣ ማህተማችንንም አንበጥስም ያሉት ከድል ነሺዎች ወገን ሲደመሩ ሥጋዊ ሞትን የፈሩ ግን ሃይማኖታቸውን ለወጡ ማህተማቸውን በጠሱ።

የሰውን ነፍስ እያጠፉ፣ ቤተ መቅደስን እያቃጠሉ ይህን እኩይ

ተግባር እንደጽድቅ ለሚቆጥሩ ሰዎች ጌታ የተናገረባቸውን ቃል ልብ እንበል። «የሚገድሏችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል» አለ። ዮሐ ፲፮:፪ በሃይማኖት ለሚ ጸኑትም ሆነ ለሚበናከሉት ሰዎች ደግሞ «ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል ስለስሜ በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናችሁ በዚያን ጊዜ ብዙዎች ይሰናከላሉ» ብሏል። ማቴ ፳፬:፱ ሰዎች ሃይማኖትን ከሚለውጡበት መንገድ እንዱ ሥጋዊ ሞትን በመፍራት ነው የምንለው ከዚህ እንፃር ነው።

1. የአጋንንትን ትምህርት በማዳመጥ

የእግዚአብሔር ልጆች ቃለ እግዚአብሔርን መማር የሚገባቸው ከእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር የተላኩ እውነተኞች መንፈሳውያን መምህራን ነው። ሐዋርያው «የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎች አይደለንምና በቅንነት ግን ከእግዚ አብሔር እንደተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራ ለን።» ፪ቆሮ፪:፲፯ ያለበት ምክንያት እርሱ ከማን እንደተማረ ስለሚያውቅ ነው። «ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም አልተማርሁትም።» ገላ ፩:፲፪ እንዲል።

ከጌታችን መማሩን የመሰከረው ሐዋርያው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት «እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው» አለ። ሮሜ፱:፭ ይህ የባሕርይ አምላክነቱ ለዘላለም መሆኑን ሲገልጽ «ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና /ቅድመ ዓለም/ ዛሬ /ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ/ እስከ ለዘላለም ያለው ነው። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ» ብሏል። ዕብ፲፫:፰ ነባቤ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም «በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር





ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ ... ቃልም ሥጋ ሆነ» ዮሐ ፩:፩,፲፬ በማለት በማያሻማ ቋንቋ ኢየሱስ ክርስቶስ አግዚአብሔር መሆኑን መሰከረ።

ይህን የባሕርይ አምላክ የአጋንንት ትምህርት ያደመጡ ወገኖች አማላጅ ነው፣ ፍጡር ነው፣ ነቢይ ነው ይሉታል። እርሱ የማስታረቁን ተግባር በመስቀል ላይ ከፈፀመ በኋላ አስታራቂነቱን ያበቃ፣ ያከተመ መሆኑን ጌታችን ሲናገር «በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ እኔም ስለእናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም።» ዮሐ፲፮:፳፮ ከማለቱም በተጓዳኝ ማስታረቁ በምድር ላይ ማብቃቱን «እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ» ዮሐ ፲፯:፬ ይህም ማለቱ አስራው ዘንድ ገንዘብ ያደረግህልኝን ሥራ ስርቼ ገለጽሁህ ማለቱ ነው። ከሁሉ በላይ በምድር የሚለውን ቃል ልብ ይሏል።

አጋንንት እና የግብር ልጆቹ ግን ይህ አማናዊ ትምህርት ስለማይስማማቸው አውነተኛውን ቃለ አግዚአብሔር በማጣመም፣ እውነቱን በሐሰት በመሰወጥ ሰዎች በጨለማ መንገድ ተጉዘው እንዲጠፉ ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡ እንደሚያስደርግ ሐዋርያው ሲያስተምር «መንፈስ ቅዱስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመናት፣ አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ» ብሏል። ፩ጢሞ፬:፩-፪ የአጋንንትን ትምህርት ማለቱን ያስተውሉ። እነዚህ የአጋንንትን ትምህርት የሚያስደምጡም ሆነ የሚያደምጡ ስዎችን ተግባር ሐዋርያው ሲገልጠው «የአምልኮ መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል ከእነርሱ ደግሞ ራቅ» ብሏል። ፪ጢሞ፫:፭

የአምልኮው መልክ በስሙ ክርስትያን ተብሎ መጠራትና በስሙ መምጣት ነው። «በስሜ ይመጣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ።»ማቴ ፳፬:፭

ጽሐፍ ቅዱስም «ኢትዮጵያ እጆቿዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች»ተብሎ ተዘግቧል። መዝ.፷፰+፴፩ ከዚህም የተነሣ ኢ ትዮጵያዊያን የራሳቸው የሆነ የአኗኗር ዘይቤ፣ አመጋገብ፣ አስተሳሰብ፣ አለባበስ ወዘተ ባህል አላቸው። በራሳቸው በሆነ ሥርዓት በሥርግ ይጋባሉ፣ ይወልዳሉ፣ ልጆች ያሳድጋሉ። ከዘመድ ወዳጆቻቸው ጋር በጣም የጠበቀ ትስስርና ማህበራዊ/ግንኙነት አላቸው። ዛሬ ላይ ግን ልጆች ቢያጠፉ እንኳ ወላጆች መክሮ ተቆጥቶ ማስተማር እየከበደ ነው። ምክንያቱም ትውልዱ የወላጆቹን ምክር አይቀበልምና። እንዲያውም በወላጆቹ ያፌዛል።«በአባቷ የምታላግጥ የእናትዋንም ትዕዛዝ የምትንቅ ዓይን የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጧታል፣አሞራዎችም ይበሉአታል» መባሉን ትውልዱ አላስተዋለውም። ምሳ.፴+፲፯ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን ወላጆች ልጆቻቸውን ከመምከርና ከመገበጽ ወደኋላ አላሉም አይሉምም።

ይህ የኢትዮጵያዊያን ተግባር መልካምና በጐ ሆኖ ሳለ በግሎባላይዜሽን ተጽዕኖ ከዚህም ሌላ አነስተኛ ቤተሰብ ቁጥር ለማምጣት ወይም ለመወሰን መገደድ የስልጣኔ ውጤት ነው ይባላል። እንዲሁም ከሰዓት ጋር ለመጓዝ በጣም ፈጣን ምግብ ያስፈልጋል በማለት የባህል ምግብ ደብዛው እንዲጠፋ አመላካች ብዥታ አለ። በሰዎች መካከል ያለውን የታላቅነት፣ የአክብሮት እይታ እየሸረሸረ ነው።በሽማግሌና በወጣት፣ በወላጅና በልጅ፣ በታላቅና በታናሽ መካከል የነበረውን መከባበርና መደማመጥ እያጠፋ አለመከባበርንና አለመታዘዝን እያመጣ ነው። አለባበሳችን ከባህላችን እየወጣ ነው። ይህን የውጭ ባህል አለባበስ ለማስረጽ ፊልሞች በጣም ትልቅ ሚና እየተጫወቱ ናቸው። እኛ የስልጣኔ ውጤት ነው እያልን ዝም ብለናል። «የባዕድ ልጆች ደለሉኝ» መዝ ፲፯:፵፬ የተባው ቃል በተግባር እየተፈጸመ ነው።





ባህል በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ቢሆንም በተፈጥሮ ባለበት የሚቆይ አይደለም ይለወጣል። ባህል የሚለወጥ ከሆነ ደግሞ ከሃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያለው ስለሆነ በሃይማኖት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ታላላቅ ሃይማኖታዊ በዓላትን፣ ንግሶችን፣ ቅዳሴ ማስቀደስን፣ በቤተ ክርስቲያን አውደ ምሕረት በአንድነት ተሰብስቦ የሰርክ ጉባኤያትንም ሆነ ስብከተ ወንጌልን ለመካፈል ጊዜ ማባከን ነው። የሚል ምልከታ እየተፈጠረ ነው። «አንድ ሆነው በልባቸው በየሕዝባቸው ኑ የእግዚአብሔርን በዓሎች ከምድር እንሻር አሉ።» መዝ.፸፫+፰ ይህ እንደተርታ ነገር በቀላል የሚታይ አይደለም። ጠቢቡ «ወይናችን አብቧልና የወይናችንን ቦታ የሚያጠፉትን ጥቃቅኑን ቀበሮዎች አጥምዱችሁ ያዙልን» ይለናል።መኃ ፪:፲፭

ዓለም እቀፋዊነት በኅብረትና በአንድነት ተገናኝቶ አምልኮን ከመፈጸም ይልቅ በማኅበራዊ ግንኙነትም ተሳስሮ አብሮ በመቀራረብ ከመኖር ወደ ተናጠል ሕይወት አኗኗር ወደ ግለኝነት የማምጣት ተጽዕኖ አለው። «ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም።» ፊልጵ:፳፩ እንዲል። በኅብረት ተሰባስቦ ሰንበቴ ለመካፈል ጽዋ ማኅበራትን ለማካሄድ ተተኪው ትውልድ እያመነበት አይደለም። ለትውልዱም «የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ»በማለት ጠቢቡ ሰሎሞን ይመክረዋል። ምሳ.፳፫+፲ ሰንበቴ፣ ጽዋ ማኅበራትና የመሳሰሉት መንፈሳዊ አገልግሎቶች በሃይማኖት ጸንቶ ለመኖር ትልቅ ድርሻ አላቸው። ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ይህን ትውፊት ከወላጆቹ መውረስ አለበት። «ጻድቅ ሰው ለልጅ ልጆቹ ያወርሳል» ምሳ. ፲፫+፳፪ እንዲል።

ከዚህም በተጓዳኝ በቤተሰብ መካከል እንኳ ሰፊ ክፍተት እየተፈጠረ ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው አስበውበት ስለ ሃይማኖት በሚገባ እንዲ

ገነዘቡ፣ ቤተ ክርስቲያናቸውን አውቀው ሥርዓቷን ትውፊቷን ተረድተው ሀገራቸውን ቋንቋቸውን ማንነታቸውን እንዲያውቁ ለማስተማር ለመከታተል እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ ነው:: ምክንያቱም «እውቀትን ጠልተዋልና እግዚአብሔርን መፍራት አልመረጡምና» ፍ

ምሳ. ፩፥፳፱

ይህ ደግሞ ማንነትን ወደ ማጣትና ወደ ምዕራባዊያኑ የባህል ተጽዕኖ ስር መውደቅን ያስከትላል:: ዛሬ ብዙ ሴት እህቶቻችን ከቀሚስ ይልቅ ሱሪ መልበስን ተያይዘውታል:: ይህ ደግሞ በተቃራኒው ጾታ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እንዳለ ሆኖ ሱሪ የሚለብሉ እህቶችን ለምን ቤተክርስቲያን አትሄዱም ሲባሉ ሱሪ ስለምለብስ ነው ብለው መልስ ይሰጣሉ:: እንግዲህ ሱሪ እንኳ ወጣት ሴቶችን ከቤተክርስቲያን ለማራቅ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው ማለት ይቻላል:: «ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ» ዘዳ፳፪:፭ በማለት እግዚአብሔር በነቢዩ ሙሴ አድሮ ማስተማሩን ልብ ይሏል::

በምዕራባዊያኑ አኗኗር፣ሥርዓት፣ አመለካከት መያዛችን በእምነታችን ላይ ቀስ በቀስ ተጽእኖ እያሳደረብን እየተሸረሸርን እንደሆነ ልብ እንበል:: «ነፍስ እውቀት የሌላት ትሆን ዘንድ መልካም አይደለም::» ምሳ.፲፱፥፪ ለራስ ብቻ ማሰብ፣ የብዙ ሰዓት ስራዎችን ለመስራት መሮጥ ወዘተ የግለኝነት አኗኗርና አመለካከት መስፋፋቱ በሃይማኖት ላይ የተጋረጠ ፈተና ነው:: ነገ ቤተ ክርስቲያንን የሚረከብና እምነቱን ስርዓቱን ጠብቆ የሚዘልቅ ትውልድ ለማፍራት አስቸጋሪ ይሆናል:: አዲሱ ትውልድ በተራው ወላጅ ሲሆን ይዞት ያቆየው እምነት ሥርዓትና ትውፊት ስለማይኖር ለልጆቹ ሃይማኖታቸውን ማንነታቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ ስለማይችል ሥልጣኔው ከጊዜያት በኋላ ሃይማኖት አልባ ትውልድ ማፍራቱ አይቀሬ ነው:: «የዚህ





ዓለም ጥበብ /ሥልጣኔ/ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነው::» ፩ቆሮ፫:፳ ዓለም አቀፋዊነት /ግሎባላይዜሽን/ በእምነታችን፣ ባህላችን፣ በአመለካከታችን ላይ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ተጽዕኖ አሳድሮ ሃይማኖት አልባ እንዳያደርገን እንንቃ:: «እንደ ጥበበኞች እንጂ ጠበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ: ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ» ኤፌ.፭፥፲፭-፲፮ ትውልዱ እንደቀደምት ወላጆቹ ሃይማኖትን ይዞ፣ ምግባርን ሠርቶ ፣በሥርዓት ተጉዞ ለሌላው የዓለም ሕዝብ በግሎባላይዜሽን ተጽዕኖ እንዳይዋጥ አርአያ መሆን ይጠበቅበታል::«ዘመኑን እየዋጃችሁ በውጪ ባሉት ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ »እንዲል ቆላ.፬፥፭

## ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ሰውን የሥነ ፍጥረት ቁንጮ አድርጐ በአርአያውና በምሳሌው ሲፈጥረው እንደ ቅዱሳን መላእክት ዘወትር በምስጋና ጽሙድ ሆኖ እንዲኖርና በኋላም ክብሩን እንዲወርስ ነበር:: ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ግን ሰው የዚህ በረከት ባለቤት እንዳይሆን የተቻለውን ክፉ ነገር ሁሉ አድርጓል:: እግዚአብሔር ወልድ የዲያብሎስን የተንኮል ስራ ካፈረሰበትና የሰውን ልጅ ካዳነ በኋላ ለዓላማው ጽኑ የሆነ ዲያብሎስ ዛሬም ሰዎች ከእግዚአብሔር እንዲለዩ ከቅዱሳን ኅብረት እንዲወጡ ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡ የማይምሰው ስርና የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም:: «ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና::» ፩ጴጥ.፭፥፰

ስለዚህ ዲያብሎስ ጥንት ቀዳማዊ አዳምን እንዴት እንዳሳተና ዛሬም ውሉደ አዳምን እንዴት እንደሚያስት፣ ዓለምን ያዳነው እግዚአብሔር ወልድንም የባሕርይ አምላክነት በመካድና በማስካድ፣ ሰዎችም ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡ የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ ላይ

ነው።«ሰይጣን በምድር ሁሉ ዞርሁአት በእርስዋም ተመላለስሁ» ብሏልና። ኢዮብ. ፩፥፯ ስለዚህ «ወንድሞች ሆይ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ ነገር ግን ከእናንተ ማንም በኃጢአት መታለል እልከኛ እንዳይሆን ቃሉ እግዚአብሔርን ለመስማት በምቶም ለመረዳት በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ የመጀመሪያ ሕ ምነታችንን እስከ መጨረሻው /እስከ ሞት/ አጽንተን እንጠ ብቅ»ተብለናል። ዕብ.፫፥፲፪-፲፬

ክርስቲያኖች ይህን እውቀው ዲያብሎስንና የዲያብሎስን የግብር ልጆች የተንኰል መረብ በመረዳት በእምነት ጸንተው ይቃወሙ ዘንድ መንገድ ለማሳየት ያህል የተዘጋጀ እነስተኛ መጽሐፍ መሆኑን አንባቢ ያን ተረድተው የጎደለውን አሟልተው፣ የተጣመመውን አቃንተው ያነቡ ዘንድ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁኝ።

«ወደ ሞት የሚነዱትን ታደግ
ሊታረዱ የተወሰኑትን አድን»
ምሳ ፳፬፡፲፩

//



# ዋቢ ምጽሐፍ


፩ መጽሐፍ ቅዱስ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤ 1980 ዓ.ም
፪ መጽሐፍ ሥነ ፍጥረት ሊቀመዘምራን ሞገስ ዕቁብ ጊዮርጊስ1987 ዓ.ም
፫ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቁ/2 ዲ/ንአባይነህ ካሴ
፬ መጽሐፈ ቅዳሴ አክሱም ማ/ቤት 1989 ዓ.ም
፭ ዳዊት መዝሙር አንድምታ ተሰፋ ገ/ሥላሴ 1982 ዓ.ም
፮ ወንጌል አንድምታ ተሰፋ ገ/ሥላሴ 1988 ዓ.ም
፯ ሥነ ፍጥረት ማኅበረ ቅዱሳን 1996 ዓ.ም አ/አበባ
፰ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ንግድ ማ/ቤ 1972 ዓ.ም
፱ ዓምደ ሃይማኖት ብርሃኑ ጎበና 1985 ዓ.ም አ/አበባ
፲ የሃይማኖት ልዩነት ከታፈስ ሙሉነህ 1997 አ/አበባ
፲፩ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ዘማኅበረ ቅዱሳን